# ይሄ ከማላቆመው መልክቶቹ ውስጥ አንዱ ነው !

**ሄኖክ የሺጥላ**

የሃገራችን ፖለቲካ ፥ ትችት እና ዘለፋ እንደ ርችት እያብረቀረቀ የሚዘንብበት የነገር ሽራተን ነው ። ትናንት ወዳጅህ የነበረ ፥ ዛሬ እንደ አማዞን እባብ ቆዳውን ሽልቅቆ ሙልጭ አድርጎ ሊሰድብህ ይችላል ፥ ሃሳብህን ሳይሆን ሱሪህን ሊያወልቅ ይፈልጋል ፥ እሱ ራሱ የወጣለት ጠንጋራ ብሄርተኛ ሆኖ ፥ ኣይኑን በጨው አጥቦ « ለምን ስለ አንድነት አትሰብክም ይልሃል » ፥የሌሎችን ቁመና ሲያፍረጠርጥ ከርሞ ፥ የሱ ቁመና ሲነካ ፥ ኣደለም ቁመናዬን እዳሪዬን እንኳ መተቸት ( መንካት ) መብትህ አይደለም ሲል አያፍርም ፥ ዲሞከራሲ አቅም የሚኖረው እና ጥያቄ ሆኖ የሚቀርበው እሱ ለሚፈልገው አላማ ሲውል ብቻ ነው ፥ ኢ ፍትሃዊነት ትርጉም የሚኖረው እሱ ሲናገረው ብቻ ነው ፥ የነፃነት ጥያቄ በሱ ልሳን ካልሆነ በሌሎች ሰዎች ልሳን መነገር የማይችል የመለኮት ቃል አስመስሎ ይቀርፅልሃል ። ሃሳቡን ፥ አካሄዱን ፥ መንገዱን እና መድረሻውን እንደ አንድ ተቆርቋሪ ዜጋ « ይህ እንዳይሆን እንዲህ ይሁን » ብለህ ስታመለክት ፥ ከግንዛቤህ ከመማር ፥ የተሳሳትከውን በጨዋ መንገድ ከማረም እና ከማስተማር ይልቅ ከ የ ፓል ቶኩና እና መሰል ቦታዎች በጋራዥ ሴል ( በብላሽ ይለዋል ጉራጌ ) የተገዙ የሳይበር ወታደሮቹን ጥቃት እንዲፈጥሙ መረጃ ይሰጣል ።

እርግጥ ይህ አካሄድ እነ ዶ/ር ታዬ ወ/ሰማትን ከሜዳ ኣስወጥቶ ሊሆን ይችላል ፥ እነ ሳይንቲስት ጥላሁን ይልማን አስደንግጦ ( ወይም ተስፋ አስቆርጦ) ይሆናል ፥ ግን ለሁሉም ይሰራል ማለት አይደለም ። ፖለቲካው ምህዋሩን በማይረቡ ሰዎች ዙሪያ ሊቀልስ ና ሲሽከረከር ስናይ ዛሬ አዲስ ኣይደለም ፥ ትናንት አዲስ ኣልነበረም ፥ ነገም አዲስ አይሆንም ። እነ አባ መላ በአንድ ጊዜ የግሎባል አሊያንስ እና መሰል ድርጅቶች ወግ ከዋኒ ሆነው ወደፊት የመጡት በእውቀታቸው ሳይሆን ባላቸው ገደብ አልባ የመባለግ ብቃታቸው ነበር ። ከነሱ የብልግና እውቀት መጠቀም የሚሻ ፥ በደካሞች መሃል ትልቅ ሆኖ መታየት የሚሻ ትንኞችን ኢየመረጠ የደረቀ ባሊ ላይ ማሰማርቱ የምንነቱ መገለጫ ነው ። እርግጥ እንደዚህ አይነት ሰዎችን ከላይ እንደገለጥኩት «በርካሽ ኪጋራጅ ሴል ላይ» ልታገኛቸው ትችላለህ ፥ ግን እንደዚህ አይነት ደካማ ፥ ነውረኛ እና አሳፋሪ ሰዎችን ወደፊት በማምጣት ለውጥ ማምጣት እንችላለን የሚል ተቋም ይሁን ኣቋቋም ለምን ተተቸሁ ብሎ አካኪ ዘራፍ ሲል ብትሰማው « ማነው ልክ » ብለህ ራስህን ትጠይቅ ይሆናል እንጂ አካኪ ዘራፉ የሰናፍጭ ቅንጣት ታህል እውነት ኖሮት ያንተን የእምነት ተራራ በፍርሃት ጨረሩ ሊገፋ እያስችለውም ።

የኛ ፖለቲካ ከሞላ ጎደል እውነትን በመፍራት እና የተናገረንን በማስፈራራት ላይ የተመሰረተ ነው ። ለራሱ ክብር የሌለው ሰው ሁለቱንም ሲያደርግ ልታየው ትችላለሁ ፥ ከዚህ ለራሱ ክብር ከሌለው ሰው ያነሰው ሰው ደሞ በዚህ ክብረ ነክ የሚደርስበትን ዘለፋ ፥ ዛቻ እና ማስፈራሪያ በመፍራት እንደ ቀንድ አውጣ ብርድልብሱ ውስጥ ተደብቆ « ፖለቲካ ለምኔ » ሲል ልታገኘው ( ልታየው) ትችላለህ ። በዚህ የመፍራት እና የማስፈራራት ትብታብ የተጠመዱት ፥ የወደቁት እና መነሳት ያቃታቸው ፥ በግሩፕ ዘለፋ ፥ በህዝባዊ ዛቻ እና በግብረ ሃይል ጥላቻ ከሜዳ እንዲወጡ የተደረጉት እና እጅ ሰጥተው የወጡት ( የወደቁት ) ፥ በኔ እይታ የአሸናፊነት ስነ ልቦና ምን እንደሆነ የማያውቁ ናቸው ፥ በኔ ግንዛቤ « ተሳዳቢው » ከኔ በኢትዮጵያዊነት ይበልጣል ብለው ያመኑ ናቸው ፥ ተቀጣሪው ወይም አቃጣሪው የተሻለ የሰውነት አቅም አለው ብለው ሽንፈትን የተቀበሉ ደካሞች ናቸው ። ይህ ግን ልክ አይደለም ።

በሃገራችንም ሆነ ከሃገራችን ውጭ ፥ ሀገራችንን በተመለከተ የሚደረግ ማንኛቸውም ሃገራዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባችንን የመሰንዘርም ሆነ ቢሆን ጥሩ ነው ብለን የምናስበውን ነገር የመናገር መብት አለን ። ይህንን መብት መለስ ዜናዊ አልሰጠኝ ፥

አያስጠብቅልኝም ፥ ይህንን መብት ብርሃኑ ነጋ አልሰጠኝም ፥ ታግሎም ኣያጎናፅፈኝም!! ይህንን መብት ከማንም ሳይሆን እንደ ሰው ከእግዚያብሄር ያገኘሁት ምንነት ነው ፥ ማንነት ነው ። ብርሃኑ ቢሳካለት ምናልባት ለተፈጥሮ መብቴ እውቅና ይሰጥ ይሆናል ፥ ባይሰጥ ግን እሱ እነ መለስን እንደተቃወመው እኔ ደሞ በተራዬ እሱን እቃወመዋለሁ ። ያንን ያህልም ተራ የምጠብቅ አይመስለኝም እንደውም !

ለሃገራቸው በየ በርሃው መስዕዋት እየከፈሉ የሚገኙ ታጋዮች በመጀመሪያ ነፃ የሚያወጡት ራሳቸውን ነው ብዬ ነው የማስበው ። የወያኔም ትልቁ ክሽፈት ራሱ ነፃ ሳይወጣ ሌሎችን ነፃ ለማውጣት መታገሉ ላይ ይመስለኛል ። የሃሳብ ነፃነትም ሆነ የመሰብሰብ መብት በድህረ ወያኔ ስርዓት የተነፈግነው ፥ እኛ ሳንሆን ወያኔ ራሱ ነፃ ስላልሆነ ነው ። እኛማ ነፃ ነን ፥ ነፃም ስለሆንን ነው የነፃ ሰው ባህሪ ያሳየነው ። የመናገርም ሆነ የመፃፍ ነፃነት የነፃ ሰው ባህሪ ነው ። ያንን ማድረግ አትችልም የሚልህ አካል ግን ያንን ነፃነት የማያውቅ እስረኛ ስለሆነ ነው ። ለዚህም ይመስለኛል ካርል ማርክስ የዘመናዊ ሰው መነጠል ( The Alienation of Modern Man ) በተባለው መጥሃፉ << The Germans toured us, used a poison gas to massacre us and even put us in a furnace, it is only because we are free>> ። የምንታሰረው ፥ ስንጥፍ የምንነቀፈው ፥ ስንናገር የምንፎተተው ፥ ስንደፍር « ኩም » አድራጊው የበዛብን እኛ ነፃ ስለሆንን ነው ። ለምን ፥ እንዴት ፥ እንዲህ ባይሆንስ ፥ ይሄ ቢሆንስ የሚል ሁል ጊዜም በእንቅልፍ ልቡ የሚኖር ስላለመሆኑ ማሳያ ነው ። ስለዚህ ሰድባችሁ የምታቆሙት ፥ አብራችሁ የምታስበረግጉት ፥ አሲራችሁ የምትጥሉት ፥ ወጥናችሁ የምታሰናክሉት ማንነት ትከሻችን አይሸከምም ። የተወሰነ ደረጃ መሄድ ትችሉ ይሆናል ፥ አራት ወይም አስር ሰዎችን አሳፍሮ ከጫወታ ውጭ ማድረግ ይቻል ይሆናል ፥ ሁሉንም ግን በአንድ አይነት መንገድ ማሸነፍ አይቻልም ። እንዲህ ያለውን ሰው ለማሸነፍ ብቸኛ መንገዱ ግን መብቱን ማክበር ብቻ ነው ።

መልክቴ ከወንዚያ ወዲህ ማዶም ወዲያ ማዶም ላላችሁት ነው ። መፃፍ ፥ ማጋለጥ ፥ ማስተማር ፥ ክርክር መፍጠር ፥ ጠያቂ እና መሪማሪ ትውልድ እንዲፈጠር የአቅማችንን ማድረግ እንቀጥላለን ። ከዚያ እኩል ተንኮሉ ፥ ሴራው ፥ ደባው እንደሚኖርም እናውቃለን ። ያፈቀሩን ለምን ጠሉን ብለን አይደለም የምንታገለው ፥ ወይም እንደ አንዳንድ ግብዞች በግሩፐ ፍቅር ሰክሮ ፥ በጋርድ እና በ ከበባ ለመሄድም አይደለም ። አላደግንበትም ። ከሊስትሮ ጋ ኳስ ተጫውተን ፥ ከቆሎ አዟሪ ጋ ተጋፍተን ነው ያደግነው ። የህዝብ ልጆች ነን ! አስተዳደጋችን አድር ባይነትን አይፈቅድም ! ማስመሰልን ደባል አድርጎ መኖር አይችልም ። ለድሃ መቆምህን ለማሳየት ስለ ድሃ ኣታውራ ፤ ከድሃ ጋ ኑር! ከድሃ ጋ ተዋለድ ፥ ከድሃ ጋ ብላ ፥ ከድሃ ጋ ጠጣ። ስለ ነፃነት መቆምህን ለማሳየት ጥቅስ አትጥቀስ ፥ አንተን ጠቅሰው ፥ ስህተትህን ነቅሰው የሚናገሩትን የማድመጥ ልምድ ይኑርህ ። ሃቀኝነትህን በምታገኘው ላይክ እና በያዝከው ማይክ ልክ አትለካው ፥ ሃቀኝነትህን ሌሎችን ለማዳመጥ ባለህ ቅንነት ልክ ለካው ! ይሄ ከማላቆመው መልክቶቼ ውስጥ አንዱ ነው !

ቸር እንሰንብት

( ሄኖክ የሺጥላ )